# የበላይነት እና ሰሜን ወሎ

[ወንድወሰን ተክሉ-ጋዜጠኛ]

**መነሻ-የሰሜን ወሎ ወቅታዊ ሁኔታ

ሰሜን ወሎ ወልዲያ፣ቆቦ፣መርሳ እና ተጎራባቾች በሀዘን ተውጠው ከወትሮው እንቅስቃሴ ከታቀቡ አስር ቀን በላይ ቢሆንም ሰኞ እለት ጥር 30ቀን 2018 የወልዲያ ከተማ በአግዓዚው ሰራዊት ለሁለተኛ ግዜ መወረራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

ሰራዊቱ ጭፍጨፋውን ከፈጸመ በሃላ በነዋሪው ጥያቄና በአቶ ገዱ ትእዛዝ ከተማዋን ለቆ እንዲወጣ የተደረገ ቢሆንም ሰኞ እለት ግን የወልዲያ ህዝብ በግፍ ለተጨፈጨፉ ወገኖቻቸው የሀዘን ጧፍ ማብራት ስነስርዓት በሚያካሂዱበት ወቅት አግዓዚው ከየት መጣ ሳይባል ከተማዋን ወርሮ በከፈተው ተኩስ የሞተ መኖሩ ባይገለጽም የቆሰለ እንዳለ ከነዋሪዎቹ አንደበት በቪ.ኦ.ኤ አድምጠናል።

በሶስቱ ከተሞች እና ተጎራባቾቻቸው ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንደሌለ -ማለትም ት/ቤቶች፣ ንግድ ተቋሞችም ሆኑ መንግስታዊ ተቋማት በሙሉ ዝግ ናቸው።በቆቦ፣መርሳና ወልዲያ በተካሄደ ጭፍጨፋ በመንግስት በኩል የተሰውትን ሰዎች ቁጥር መግለጽ አልተቻለውም። አቶ ንጉሱ ጥላሁን የአመራ ክልል መስተዳድር ቃለ አቀባይ ስለጠፋው ህይወት ማዘናቸውን ቢገልጹም የማቾቹን ቁጥር ለመግለጽ ግን አልደፈሩም።

ጥርት ያለ መረጃ ለማግኘት አዳጋች ቢመስልም ከነዋሪዎቹ አንደበት በመነሳት በሶስቱ ከተሞች ከ30በላይ ንጹሃን [አንዳንድ መረጃዎች ቁጥሩን ከ50በላይ ያደርሱታል]መሰዋታቸውን ማወቅ ይቻላል።

የወደመው መንግስታዊ፣ድርጅታዊና ግለሰባዊ ተቋማት እጅግ በርካታ ነው። በአግዓዚው ሰራዊት የቤት ለቤት አሰሳ የታሰሩት ቁጥር በመቶዎች ይቆጠራል። ቁጥሩን ለመግለጽ ያዳገታቸውን እና የጠፋውን የሰው ልጅ ክብር ህይወት የሚተካ ባይኖርም ወደሙ ስለተባለው ተቋማትና ንብረቶች መተካት መቻል ለጥያቄ የሚያበቃ ባለመሆኑ የአትኩሮታችን ትልቁ አቅጣጫ ለምን ይህን ያህል የሰው ልጅ ህይወት እንዲጠፋ ተደረገ የሚለው ላይ ይሆናል።

ለምንድነው ይህን ያህል ቁጥር [ቁጥሩ የተደበቀው የተሰውት ሰዎች ቁጥር ብዙ በመሆኑ እንደሆነ ነዋሪዎች ይገልጻሉ]ክቡር የሰው ህይወት እንዲጠፋ ሆን ተብሎ ጭፍጨፋ የተፈጸመው?ለምንድነው ሰሜን ወሎ የጭፍጨፋው ኢላማ የተደረገችው? ዛሬ ሰሜን ወሎ የተመረጠች ቢመሰለንም ህወሃት ግን ተመሳሳይ ብሄር ተኮር ጭፍጨፋን በጎንደር፣በምስራቅ ኦሮሚያ፣በባህርዳር፣በቡኖ በደሌ፣ በጋምቤላ፣በአፋር፣በቤኒሻንጉልጉምዝ፣በመተከል፣በኦጋዴን፣በኮንሶና ..ወዘተ ስፍራዎች ፈጽሟል ዛሬም እየፈጸመ ነው።

እናም ዛሬ እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ ህዝብም ሆነ እንደ ሀገር ክፉኛ የታመምንበት ወቅት ነው። ህልውናችንን ለአደጋ ለመስጠት ሃይልና ጉልበትን ተጎናጽፎ ለህመም የዳረገን ቫይረስ የበላይነት የወለደው ዘር ተኮር ጭፍጨፋ፣ጥቃትና ግጭት ነው።

በመጀመሪያ ህወሃት የበላይነትን ወለደ። የበላይነትም በተራው ጎሰኝነት የተባለውን ሃይለኛ ቫይረስ ወለደ።

ዛሬ በዚህ ቫይረስ እኛ ክፉኛ እየተበላን ያለን ህመምተኛ የሆንን ህዝብ ሆነናል። ሆኖም ይህንን ቀርጣፊ ቫይረስና የቫይረሱን ተሸካሚ በማርከሻ መድሃኒት ታክመን መዳን ይገባናል ብዬ አምናለሁ። መድሃኒታችንም ያለው ህዝባችን ውስጥ ነው።

*** በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ግጭቶችና ጥቃቶች ሁሉ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ናቸው

ያገባደድነው ሳምንት የሰሜን ወሎ ዞን ወደ ለየለት የጦር ቀጠናነት የተለወጠበት መሆኑን ያስተዋልንበት ሳምንት ሆኖ አልፎዋል። በእርግጥ ሳምንቱ ያለግዜያቸው ለህልፈት የታዳረጉ በርካታ ሰዎችን ህይወት ነጥቆ ያለፈ ቢሆንም ማንነት ላይ በማነጣጠር የተለኮሰው የጥቃት እሳት ግን ዛሬም እየተንቀለቀለ ያገኘውን ሁሉ የሚለበልበው ይህ ጦርነት ካሳለፍነው ሳምንት ጋር ሳያልፍ ወደዛሬው አዲስ ሳምንት ተሸጋግሮ ያለመሆኑን ከተግባራቱ እያየነው ያለ እውነታ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ብሄር ተኮር ጥቃት በሁለት ነገዶች መካከል አንዱ ሌላኛውን ለማጥፋት እያካሄደ ያለ ጥቃት ሳይሆን በገዢው ህወሃት በኩል የወለደውን የበላይነት ሙሉ በሙሉ ለማሳደግ እየመረጠ የሚፈጽመው ብሄር ተኮር ጥቃት ነው ህዝብንና ሀገርን እየጎዳና ወደ አደገኛ እየመራን ያለው።

ዜጎች በምግባረ ስራቸው ሳይሆን በማንነታቸው ብቻ ይገደላሉ፣ በግፍም ከርስት ቀዬአቸውም እየተነጠቁ ይፈናቀላሉ፣ ያለወንጀላቸውም ተከሰው ይታሰራሉ፣የንግድ ተቋሞቻቸውንም ያለርህራሄ ይነጠቃሉ፣ብሎም ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ ይገደዳሉም።

በእርግጥ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ግድያና ጥቃት ብቻ ሳይሆን እየደረሰባቸው ያለው ሹመትና ሽልማት፣ስልጣንና ሀብትም  ጭምር በችሎታና በአገልግሎታቸው ሳይሆን በማንነታቸው ብቻ እየተሰጣቸው ያለበት ወቅት ላይ እንዳለን ግልጽ ነው።

ከእንጨትም መርጦ ለታቦት እንደተባለው ህወሃት ከነገድም የተለየ ያለውን ነገድ ለንግስና እና ለሁለንተናዊ የበላይነት ሲመርጥ ከዚህ በተጻራሪ መልኩ ደግሞ ለጭቆና፣ለብዝበዛ፣ለበታቸኝነት እና ለጠላትነት ሊመረጡ ይገባል ያላቸውን ነገዶችንም በዘርፍ ዘርፉ ለይቶና መርጦ እርምጃ በመውሰዱ ላይ ሲያተኩር ይታያል።

የህወሃት ማንነት ላይ ያነጣጠረን ጥቃትና ጭቆናን ምንጭ ስንፈልግ በድርጅቱ አፍላ እድሜ ላይ እያለ የጸነሰውና ስልጣን ከያዘ በሃላ የወለደውን በኢትዮጵያዊያን ላይ የድርጅቱን እና "እወክለዋለሁ" የሚለውን የትግራይን ህዝብ "የበላይነት "የተባለን ዓላማ ለወግ ማእረግ ለማብቃት በሚያደርገው ግብግብ የተፈጠረ ተግባር ሲሆን የአጸፋ መልስንም መፍጠር መቻሉንም ማየት ጀምረናል።

ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ ያለው ህዝብ በጨቃኙ ህወሃት መራሹ ስርዓት ጥቃት ላይ የአጸፋ ጥቃትን በድርጅቱ፣በድርጅቱ ደጋፊና በድርጅቱ ነገድ አባላትም ላይ ንብረታቸውን በማውደም ሰዎቹንም በማግለልና በመነጠል በህወሃት በተቆፈረው መለያያ ቦይ ውስጥ ይጓዝበትም ጀምራል።

ሰሞኑን ግን በሰሜን ወሎ በታወቁት ሶስት ከተሞች ህዝቡ አጸፋውን የመለሰው ለጥቃቱ ሚና አላቸው ያላቸውን ሲሆን ሰለባዎቹም የአማራና የትግራይ ተወላጆች ሆነው ተገኝተዋል።

ህወሃት ድርጅታዊ ተቋሙን እና "እወክለዋለሁ" ...[ህወሃት በትግራይ ህዝብ የተመርጠ ተወካይ ሳይሆን በእያንዳንዳችን እራስ ላይ ያለምርጫችን እና ውዴታችን በሃይል ፊጥ እንዳለ የትግራይንም ህዝብ ከደደቢት ጀምሮ በመሰሪ ሴራና ደባ በሃይል አስገድዶ እንደተፈናጠጠ የድርጅቱ ቀደምት አባላት እንደነ ገብረመድህን አርዓያ ህያው ምስክር ናቸው። እናም ተወካይ ነው ብዬ ስለማልቀበል ነው በኮቴሽን እየገለጽኩት ያለው] ..የሚለውን የትግራይን ህዝብ በኢኮኖሚ፣በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በሁሉም መስክ በተቀረው ህዝብ ጫንቃ ላይ የበላይ እና ሃያል ገዢ አድርጎ ለመገንባት የሚያደርገው መሰሪ ተግባር ማንነትን መሰረት አድርጎ ለተፈጠረው ጥቃት አስኳል ሆኖ የፈጠረ መሆኑን እያየን ነው።

ለዚህ ኢ-ፍትሃዊ ለሆነው ቅዠታዊ ህልሙ ተፈጻሚነት "እንቅፋት ይሆኑኛል"ያላቸውንም ነገዶች በማንነታቸው ብቻ እየነጠለ የማጥቃትና የማስጠቃትን ተግባር በጥልቀትና በጭካኔ እያጧጧፈው እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይህ የአንድን ገዢ ሃይልና ነገድ በሌላው ህዝብና ሀገር ላይ የበላይ ገዢ አድርጎ መፍጠር የሚቻለው የበላይነትን የቋመጠው ሃይልና ወገን የበላይነቱን ሽቅብ አጉልቶ የሚያሳያሉትን የበታቾቼ ናቸው የሚላቸውን ክፍል በመፍጠር እንደሆነ እንረዳለን።

ምን ለማለት ነው-ዓለምን መግዛት ያለበት በምርጥነቱ ከተቀረው የዓለም ህዝብ ብቻ ሳይሆን ከሀገሬውም የበለጠ ምርጥ የሆነው የአርያን ዘር ነው እያለ ጀርመናዊያንን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአራት ሃያላን ሀገራት እንዲወረሩና ክብራቸው ተዋርዶ ሀገራቸውም እንድትንኮታኮት ያደረገውን የናዚ ስርዓትን ተግባር ለአብነት እጠቅሳለሁ።

የበላይነት የሚለው ቃልና መንፈስ ትርጓሜው በሌሎች ብዙሃን ላይ የበታችኝነት ጭኖ እራሱን ሽቅብ የሚያንጠራራ እንደሆነ ይታወቃል።
በግዛቷ ጸሐይ የማትጠልቅባት የተባለላት የታላቋ ብሪታኒያ "ታላቅነት" የስንት ሀገራትን ሉዓላዊ ህልውናን ጨፍልቆና የበታች አድርጎ እንደተነገረለት ከታሪክ እንደተማርነው ሁሉ በዘመናችን ደግሞ የአሜሪካ ትቅደምን መፈክር መሪ ዓላማቸው አድርገው የተነሱት ዶናልድ ትራምፕ ሀገራቸውን ቀዳሚ የበላይ ለማድረግ የተቀረውን ዓለም ደፍቆ በመቅበርና የበታች በማድረግ ስለሆነ ዓለም በተለይም ከወዳጆቻቸው አውሮፓዊያን በኩል -የገጠማቸውን ታላቅ ተቋውም በዚህ የአንድ ዓመት ቆይታቸው እያየን ነው።

በስልጣኔ እውቀትና በሀብት ክምችት ከሌሎች ልቀው የሚወጡ ፍትሃዊ "የበላዮችን" የዓለም ማህበረሰብ በጸጋ እየተቀበለ ቢያስተናግድም ኢ-ፍትሃዊ የሆነን የበላይነት [ማለትም በሌላው መስዋእትነት፣ዋጋ ከፋይነትና የበታች ሆኖ ተረጋጭነት ላይ የሚፈጠር የበላይነት ማለቴ ነው]በተቀረው ህዝብ እና ሀገር ላይ ለመጫን የተነሱ ሃይሎች ሁሉ በተነሳባቸው የበታች አንሆንም ባይ ህዝብ ዓመጽ አይሆኑ አወዳደቅን እየተንኮታኮቱ ሲወድቁ ሰምተናል -ወይም አይተናልም።

"እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትኖ ወርቅነቱን እንዳሳየ -በታላቅ ችግርና ፈተና ተፈትኖ ወርቅነቱን ካስመሰከረው የትግራይ ህዝብ አብራክ በመወለዴ እጅግ እኮራለሁ" የሚለው የማቹ አቶ መለስ ዜናዊ እምነት ግላዊ ሳይሆን የሚመሩት ድርጅት ህወሃት ህግና መመሪያ በመሆን ህወሃት ለሚያራምደው የበላይነትን መፍጠር ዓላማ አንቀሳቃሽ ሞተር ህኖ የሚመራው እንደሆነ ይታያል።

የናዚው "ምርጥና የተለየው የአሪያን ዘር"ፍልስፍና ከህወሃቱ "ወርቅ ከሆነው የትግራይ ህዝብ" አገላለጽ ጋር ያለው ልዩነት የስፍራና የቃላት ካልሆነ በስተቀር ሁለቱም ሃይሎች እንወክለዋለን

ያሉትን በጀርመን የአሪያን ዘር ተወላጆችን -በኢትዮጵያ የትግራይን ህዝብ ከተቀረው የሀገሬው ህዝብ ለይቶና በሁሉም ዘርፍ የበላይ አድርጎ ለማውጣት አልመው የሚጥሩ ተመሳሳይ ሃይሎች መሆናቸውን ነው የምናየው።

[እዚህጋ መታወስ ያለበት የትግራይ ህዝብ ለበላይነት እየታገለን ነው እያልኩ ሳይሆን ህዝቡ ቢፈቅድም ባይፈቅድም ተወካዩ ነኝ የሚለን ህወሃት ለከት የለሽ የበላይነትን በተቀረው ህዝብ ኪሳራና ክፍያ እየገነባ ነው ለማለት እንደሆነ ግንዛቤ ይያዝልኝ]

ማነው የበታቸኝነትን ለእኔ የሚመጥነኝ ስፍራ ነው በሚል ተቀብሎ የባርነትን ህይወት በዝምታ የሚኖረው?

ጎሳን ተንተርሶ የሚፈጸመው ጭፍጨፋና ጥቃት የበላይነቱን ለማሳወቅ በተነሳው ሃይል ላይ የበታቸኝነትን እጣፈንታ አልቀበልም ብሎ በሚያምጸው ሌላኛው ወገን ላይ የሚወሰድ ዘር ተኮር እርምጃ ነው።

በበላይነት ላይ የሚያምጹ የአንድ ሀገር አጠቃላይ ነገዶች ላይሆኑ ይችላሉ ። ለምሳሌ በጀርመን ለናዚ የበላይነት ቅዠት በችሎታቸው ምክንያት አስጊ ተብለው የተፈረጁትን አይሁዶችን ነጥሎ የማጥፋት ተግባር የፈጸመ ሲሆን በሀገራችን ደግሞ ለህወሃት የበላይነት ቅዠቱ ትልቅ አደጋ ተደርጎ የታየው የአማራውና የኦሮሞን ነገድ ከተቀሩት 79 ነገዶች ነጥሎ ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት ላለፉት 26ዓመታት እጅግ ዘግናኝ ወንጀሎች በሁለቱ ነገዶች ላይ ሲፈጽም ይታያል።

ነገር ግን ህወሃት ይህን ድርጅታዊ ተቋሙን እና "እወክለዋለሁ"የሚለውን የትግራይን ህዝብ የበላይነትን በተቀረው ኢትዮጵያዊ አናት ላይ ለማንገስ በሚያደርገው ዘመቻ ማንነትን መሰረት አድርጎ እያጧጧፈ ባለው ዘር ተኮር ጥቃት ከተጠቂውም ሆነ የህወሃት ጥቃት ሰለባ ካልሆነውም ወገን ..[የጥቃት ሰለባ ያልሆነውም የሚለው አባባል ድርጅቱ በ1968 ባወጣው በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ጨቋኝ የአማራ ነገድ የትግራይ ህዝብ ጠላት ስለሆነች እረፍት አንሰጣትም በማለት በይፋ ጦርነት ካወጀበትና አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በሃላ ደግሞ የኦሮሞን ነገድ አካትቶ እያደረገ ካለው መጠነ ሰፊ ዘመቻ ጋር በማነጻጸር እንጂ በህወሃት ያልተጠቃ ወገን አለ ለማለት እንዳልሆነ ከግንዛቤ ይወሰድልኝ] ..ተመሳሳይ የአጸፋ እርምጃን መፍጠሩ መካድ የማይቻል እውነታ ነው።

ላለፉት ሁለት ዓመታት በተካሄደው ህዝባዊ ዓመጽ የህወሃት ንብረት በሆኑ ተቋማት ላይ እየተነጠለ እርምጃ ሲወስድ ታይቷል። የህወሃት መፍለቂያ የሆነችው ትግራይ ተወላጅ የሆነ በተቀረው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለው አመለካከት የፍቅርና የአብሮነት ሳይሆን የጥርጣሬና ብሎም ነጥሎ የማግለል እርምጃን ሲያስወድ በገሃድ ታይቷል።

በአንዳንድ የአማራና ኦሮሞ ግዛቶች የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸው ብቻ እንጠቃለን በሚል ስጋትና ፍርሃት ህዝባዊው ዓመጽ ባየለባቸው ስፍራዎች ለቀው ለመውጣት እንደተገደዱ ታይቷል። ህወሃት በፕሮፖጋንዳነት ከተጠቀመበት አንዱ በጎንደር የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸው ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ተፈጸማባቸው በማለት በአይሮፕላን ወደ መቀሌ የተመለሱትን እና ተፈናቅለው ወደ መተማ የተጋዙትን ታሪክ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

በቅርቡ ደግሞ በአዲግራት ዩንቨርሲቲ የአማራ ተወላጅ መገደል በሃላ በወለጋ ሶስት የትግራይ ተወላጆች መገደላቸውን እናውቃለን። በስርዓቱ በኩል በአማራውና በኦሮሞው ላይ በማንነቱ ምክንያት ብቻ የጭፍጨፋ እርምጃን መፈጸምን እና ማስፈጸምን ….[ይህን ስል ምን ለማለት ነው- ለምሳሌ በምስራቅ ኢትዮጵያ ለዘመናት ተከባብረውና ተፈቃቅረው በሚኖሩት የኦሮሞና የኦጋዴን

ህዝብ መካከል ግጭት የተነሳ በማስመሰል በክልሉ ልዩ የፖሊስ ሃይል በኦሮሞ ተወላጆች ላይ በከፈተው ጭፍጨፋ ከ700ሺ.ህ በላይ የኦሮሞ ተወላጆች ለመፈናቀልና በሺ.ህ ለሚቆጠሩት ህልፈተ ህይወት ዋና አዛዥና አስፈጻሚው ህወሃት ቢሆንም ፈጻሚው ግን በአብዲ ኢሌ የሚመራው ልዩ ፖሊስ ሃይልን መሰል እርምጃን ለመግለጽ ነው]....ስራዬ ብሎ መፈጸም የተለመደ ሲሆን በተጨፍጫፊው ህዝብ በኩል ደግሞ በአጸፋው የህወሃት ነክ ንብረትና ተቋማትን ብሎም በውስን የትግራይ ተወላጅ ንብረት ላይ እርምጃ መውሰድን እለት በእለት እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ሲሄድ አይታይም።

የተጠናወተውን የበላይነት በሽታ እንደያዘ በስልጣን ላይ የሚራዘም ከሆነ ላለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ካየነው ነገድ ተኮር ጥቃት[በምስራቅ፣በኢሉባቦር፣በጎንደርና በወሎ ውስጥ እንደተፈጸመው ማለት ነው] ነገ ተነገወዲያ እጅግ የባሰ ጭፍጨፋና ጥቃት መፈጸም ስለመቻሉ ሁኔታ ለመናገር ጠንቋይ መሆን አያሻም።

የብሄር ተኮር ጥቃት በተመሳሳይ ሁኔታ ብሄር ተኮር የአጸፋ እርምጃ እንደሚፈጥር ሳይንሱም ሆነ የሰው ልጅ ስነባህሪይ በግልጽ እያስቀመጠ ሳለ ህወሃት ግን ወገን አልባ የሆነ ይመስል ሌላውን ወገን በዘሩ ምክንያት ሲገድልና ሲያፈናቅል የበላይ አደርገዋለሁ የሚለውን የትግራይን ህዝብ ጠላት እየሸመተለትና እየፈለፈለለት መሆኑን ለትግራይ ህዝብ ነጋሪ ያሸዋልን? እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ።

ህወሃት ግን ይህን የትግራይን ህዝብ ከተቀረው ህዝብ ጋር እሳትና ጭድ እንዲሆን ሆን ብሎ እያደረገው ነው ስል በሁለት ዋና ምክንያቶች ሲሆን-

1ኛ-የራሱን ስልጣን ጠባቂና ተንከባካቢ ለማድረግ

2ኛ-የህወሃትን 50ኛ የምስረታ በዓልን በነጻይቱ የትግራይ ሪፐብሊክ ነው የሚከበረው ለሚለው ቅዠታዊ ዓላማው ማስፈጸሚያነት ለማመቻቸት ብሎ እንደሆነ እንረዳለን።

ማንነት የተፈጥሮ ስጦታ እንጂ የግል ምርጫ አይደለም። የሰው ልጅ በማንነቱ ኮርቶ መመጻደቅ እንደማይቻለው ሁሉ በዚሁ ማንነቱም አፍሮና ተሸማቆ ለጥቃት መጋለጥም ሆነ መጠቃት ክቶም ቢሆን አይገባም።

የሰው ልጅ የሚመዘነው፣ መኩራትም ሆነ ማፈር ካለበት በስራ ምግባሩ ሆኖ ሳለ ያለምርጫው ግን በተፈጥሮ መራጭነት ከአማራው፣ከኦሮሞው፣ከትግሬው፣ከጉራጌው...ወዘተ ነገድ ስለተወለደ ብቻ በወንጀል ፈርጆ ማጥቃትም ሆነ መሸለም ምክንያታዊ ነው ከተባለው ጤናማው የሰው ልጅ አስተሳሰብ የሚጠበቅ አይደለም።

እናም ህወሃት ላለፉት 26ዓመታት በወሳዳቸው ህወሃትን እና የትራይን ህዝብ የበላይ የማድረግ ዘመቻው እስከዛሬ ጎልቶ የተሳካለት በተቀረው ኢትዮጵያዊ እና በትግራይ ህዝብ መካከል ግንብ ሆኖ የሚለያይ ልዩነትን የፈጥረ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በኦሮሞና አማራ መካከል፣ በኢትዮጵያዊያን እና በኢትዮጵያዊነት መካከል የገነበው የልዩነት ግንብ ተንኮታኩቶ የፈረሰበት ሲሆን ለጊዜው በትግራይ እና በተቀረው ህዝብ መካከል የገነባው ልዩነት ግንብ በመለያየት ተግባሩ ተጠምዶ እንደተገተረ ነው የምናየው

***የሰሜን ወሎ ጥቃት/ጭፍጨፋ በማንነት ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ማሳያዎች

ከሳምንት በፊት በመላ ኢትዮጵያ የጥምቀት ክብረ በዓል ሲከበር በወሎዋ ወልዲያ ብቻ ለምን የፖለቲካ ዘፈን ትዘፍናላችሁ ተብለው በርካታ ንጹሃን በግፍ ቅዱስ ጽላቱ ፊት ለፊት ተገደሉ፡ በጥምቀት እና ገናን መሳይ የህዝብ ዓመታዊ ክብረ በዓላት ላይ እጅግ በሚፈሩትና በሚከበሩት ንጉስ ሃይለ ስላሴ ዘመን እንኳን ንጉሱን የሚተች ይዘፈናል፡

ታቦት ሊያነግስ የወጣ ህዝብ በዚህ በዓል ላይ ጸረ መንግስት መንግስት ዘፈን ዘፈንክ ብሎ የ13ዓመቱን እምቦቆቅላ ታዳጊ ዮሴፍ እሸቱን ጨምሮ ከ20 በላይ ንጹሃን ክርስቲያኖችን በግፍ መግደል አጠፉ ከተባለው ዘፈን ጋር ተመጣጣኝ ነውን?

በመጀመሪያ ይህ ህዝብ የዘፈነው ጸረ መንግስት ዘፈን ነው ብለን እንመን፡ እሺ ዘፈኑ፡ የት ነው የዘፈኑት ? በጥምቀት በዓል እለት በሰሜን ወሎ ወልዲያ በምትባል አነስተኛ ከተማ ነው እንደዘፈኑ እንረዳለን።

እሺ -ይህችስ ከተማ ማነች?የሀገሪቱ ገዢ መቀመጫ መዲና የሆነችና ቤተመንግስቱን ያቀፈች ከተማ በመሆን ለመንግስት የምታሰጋ ነችን ? ብለን ስንጠይቅ-አረ በፍጹም ።አይደለም ዋና ከተማ የሆነች ይቅርና የአማራው ዋና ከተማ ያልሆነች፣እጅግ አነስተኛ ከተማ በመሆና የህዝቧ በጥምቀተ ባህሯ ጸረ መንግስት ዘፈን የመዝፈኑም ሆነ አለመዝፈኑ ለመንግስት ተብዬው ገዢ ስርዓት ምንም ዓይነት የደህንነት ስጋት አያመጣም የሚል መልስ እናገኟለን።

ታዲያ ለምንድነው ታቦቱ ፊት "ለምን የፖለቲካ ዘፈን ትዘፍናላችሁ "ብሎ ከ20 የበለጡ ንጹሃንን አግዓዚው በግፍ የገደለው ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ የወልዲያ፣የቆቦና የመርሳ ህዝብ በጥይት እንዲቆላ ያስቻለውን እጅግ ታላቅ ጥፋትና ወንጀል እናገኟለን።

አዎን-የወልዲያ፣ቆቦና መርሳ ህዝብ ይህንን አሰቃቂ ወንጀልና ጥፋት ባይፈጽሙ እንዲህ አይጨፈጨፉም በማለት በጨፍጫፊው አግዓዚ እርምጃ ትክክለኟነት ላይ ድምዳሜም እንሰጣለን ማለት ነው።

የዚህ ህዝብ ታላቅ ወንጀልም አማራነቱ እንደሆነ እነግራችሃለሁ።
አማራነት ወንጀልና ሃጢያት ነው በህወሃቱ መጽሃፈ ቅዱስ። አማራ ሆኖ መወለድ ጥፋትና ከፍተኟም ወንጀል ነው በዚህ በህወሃቱ የ1968ማንፌስቶ መጽሃፈ እርኩስ።

በወልዲያል፣ቆቦ፣መርሳ እና ተጎራባች ያሉ አማሮች በጎንደር ወልቃይት ጠገዴ፡በሰሜን ሸዋ መንዝ፡ደብረብርሃን እና አንኮበር እንዲሁም በጎጃም መተከል እንደተወለዱትና በህወሃት እንደተገደሉት አማሮች ከወንጀለኛው አማራ የተወለዱ በመሆናቸው ይህ ወታደራዊ የወረራና የጭፍጨፋ ዘመቻ በጀግናው ህወሃት የተወሰነባቸው ናቸው።

*** ይህንን ዘር ተኮር ጥቃት እንዴት እናስቁም-? የተላላፊው ቫይረስ አደጋ-

ህወሃት የወለደው የህወሃት የበላይነት ልጅ ቫይረስ የሆነው ጎሰኝነት የበላይነቴን ይነጥቁኛል፣ ያደናቅፉብኛል ወይም ያግዱብኛል ብሎ የፈረጃቸውን ቁጥር 1 ቁጥር 2 እና ቁጥር 3 ብሎ የፈረጃቸውን ነገዶችን የማዳከም፣የመሰባበርና ብሎም በመጨረሻ ላይ አመንምኖ በማጥፋት ቀሪዎቹን ታዛዥና ተጋላቢ ለማድረግ በግልጽ፣በስውርና በእጅ አዙር ጥቃት እያጠቃ ነው-ዛሬም ነገም ከማጥቃትና ከማስጠቃትም ወደ ሃላ አይልም።

ጥቃቱ ግን አዙሪት አለው።
እጅግ በፍጥነትም ተላላፊ ከመሆኑ የተነሳ ለጥቃት የታጨውና የተመረጠው ነገድ በአጸፋ እርምጃ የአጥቂውን ወገንና ነገድ እንዲያጠቃ የሚያደርግ ተላላፊ ቫይረስ ነው። የደም ነገር ደም ያፈላል እንደሚባለው ወገኑ የተገደለበት ቤተሰብ አባል የገዳዩን ቤተሰብና ዘመድ አባል ግን እጅግ ንጹህ የሆነም እንኳን ቢሆን አሳዶ በመድፋት ደም መመለስ ባህልና ባህሪይ በሆነበት ማህበረሰባችን ውስጥ በህወሃት ጸነሽነት የተወለደውና የተዘረው ይህ ነገድን መሰረት ያደረገው ጥቃትም ሆነ ሹመትና ሽልማት ሁኔታ ወደድንም ጠላንም ሀገራችንን ወደ ኪጋሊ አቅጣጫ እያስከነፋት እንዳለ መረዳት ይኖርብናል።

የህወሃት ጎሳ ተኮር አጠቃላይ እርምጃ ኢትዮጵያን ወደ ሩዋንዳዋ ኪጋሊ ከተማ እያስገሰገሰ ሲሆን በዚህ ጉዛዋም ሀገራችን የኬኒያን ግዛት አልፋ የዩጋንዳንም ግዛት አጋምሳ የሩዋንዳን ግዛት ከአድማስ ባሻገር ማየት ጀምራለች።

የሀገራችን ጉዞ ካልተገታና በዚህ አሁን በምትጋዝበት አቅጣጫና ፍጥነት ከተጋዘች የሩዋንዳን ግዛት የምትረግጥበት ግዜ እጅግ እሩቅ አይደለም።ሩዋንዳ ማለት ይሩዊ ዘር ተኮር ጭፍጨፋ የሚፈጸምበት ግዛት በመሆን እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ህዝብ እኛን ኢትዮጵያዊያንን የሚያንኮታኩት እንጂ የሚጠቅመንን የምናገኝበት ስፍራ ስላልሆነ እያንዳንዳችን የዚህን ቫይረስ አደገኝነትን አውቀን ቫይረሱንና የቫይረሱን ተሸካሚ [ህወሃት ነው]ከማህበረሰባችን የምንነጥልበትን ግላዊም ይሁን ቡድናዊ ፣ነገዳዊም ይሁን ሀገራዊ የጋራ ስልትና መንገድ በመቀየስ የነገን ሁኔታ ዛሬ ላይ ማስቀረት ይኖርብናል።

የዚህ ቫይረስ ማረከሻ መድሃኒቱም ከባህር ማዶ የሚመጣ ሳይሆን በይዝባችን ውስጥ ያለና በተለየ ሁኔታ የመድሃኒቱ አስኳል በኦሮሞው፣አማራውና በትግሬው ህዝብ እጅ እንዳለ ልናውቅ ይገባናል።

በእነዚህ ሶስት ነገድ ህዝብ እጅ ላይ ያለው ወሳኝ ቁልፍ ሚና የ78ነገዶችን እና የሀገሪቷን ህልውና አደጋ ላይ ከጣለው የህወሃቱ የበላይነት ወለድ ቫይረስ ሊታደግ የሚያስችለውን መድሃኒት እንደያዘ እረዳለሁ።

ናዚዎችና የጣሊያኑ ፋሺስቶች ለጀርመን እና ለጣሊያን ህዝብ የተለዩ ተቆርቃሪ መስለው በመንገስና በማስተባበር የሁለቱንም ሀገሮች ህዝብ ክፉኛ አስጨፍጭፈዋል-አንኮታኩተውም እንዲፈራርሶ አስደርገዋል።

ዛሬ የትግራይ ህዝብ እጅግ ወሳኝ በሆነ ታሪካዊ መንገድ ላይ ያለ ህዝብ ሆናል። የቀረበለት ምርጫ የጀርመንና የጣሊያን ፋሽስቶች ዓይነት ምርጫ ነው። በስሙ እየመለ እየተገዘተ-ከአብራኩ በመወለዱ እንደሚኮራና የትግራይ ህዝብን ለታላቅነት ለማብቃት ብቸኛው ሃይል እሱ እንደሆነ እየገለጸ ያለውን ግን የህልውናችንን መሰረት እያፈራረሰ ያለውን የህወሃት ቡድን ለይቶ ማየትና የወደፊቱን ህልውና ማዳን ይኖርበታል።

የተለየና ልዩ ጥቅም፣ልዩ ክብር፣ልዩ መብትና ልዩ ስልጣን አመጣልሃለሁ የሚል ሁሉ እጅግ ልዩ ጥፋት፣ልዩ ውድመትና ልዩ እርግማን አመጣሁብህ እያለህ እንደሆነ የትግራይ ህዝብ መረዳት ይኖርብሃል።

ሲጀመር-በአንዲት ሀገር ውስጥ በርካታ ነገዶች ባሉበት እንዴት ሆኖ ነው አንደኛው ከሌሎች የተለየና ልዩ ጥቅም፣መብትና ስልጣን ይገበዋል ተብሎ የሚታሰበው?

የህወሃት ታላቅ ጥፋት መነሻው ይህ ነው። ለትግራይ ህዝብ እጅግ ተቆርቋሪ፣ብቸኛ ተሚጋች፣ ብቸኛ ጠባቂና ልዩ ጥቅም አስከባሪ አድርጎ ህዝቡን ጋርዶም፣አታሎም ይሁን አስገድዶም እንዲከተለውና እንዲያመልከው ማድረግ ነው።

ዛሬ የትግራይ ህዝብም ሆነ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃት በወለደው በዚህ የህወሃት የበላይነት ቫይረስ የተነሳ ግስግሴያችንን ወደ ሩዋንዳዋ ኪጋሊ አድርገናል- ማንም በተለይም ህወሃት የሚያተርፍበት ሳይሆን የሚንኮታኮትበት ግዛት በሆነችው ሩዋንዳ ከመግባታችን በፊት እንቆጣጠረው ዘንድ የበኩልህን ሚና ልትወጣ ይገባል ስል እገልጻለሁ።

ቸር እንሰንብት!

------------------------

መል እክታችሁን በኢትዮሚዲያ ኢ-ሜይል ወይም በግሌ teklu7@gmail.com ብትጽፉ እመልሳለሁ